# መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎችን በነፃ እያደሉ ያሉት ተስፋዬና ግብረ አበሮቹ ናቸው

**ዮናስ (ክፍል 2)**

የወሰድነው ፋታ የተስፋዬን መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎች በደንብ ለማጣጣምና ለማብላላት አጋጣሚ እንደፈጠረልን እገምታለሁ። ይህም ብቻ ሳይሆን ግብረ አበሮቹ ያልኳቸው እነ አቤ ቶክቻውም ፍትህ ጋዜጣ ላይ በነበረው አምዳቸው ሲያድሉን የነበረውን መርዝ የተቀባ ከረሜላ ለማስታወስ መሞከራችንም አይቀርም። ስለሆነም ስለአጀንዳችን መረዳት ጠቃሚ የነበረ ፋታ ነው ስል እወስዳለሁ።

አቤ ቶክቻውን ከአውራምባ ታይምስ ጀምሮ በፍትህ ጋዜጣና አሁን ደግሞ በየድ ረገጹ ላይ እንዲሁም በፌስ ቡክ አድራሻው በሚለቀው ጽሁፍ እናውቀዋለን። አቤም ልክ እንደ ተስፋዬ መርዘኛ ቃላቶቹን በጨዋታ ለውሶ መወርወርን ተክኗል። ቋንቋ አጠቃቀምን ይችልበታል። ቃላት አደራደሩም ለሾሃማ ነገሮቹ በጅተውታል። ጫፍ ይዞ መተርተርን ተጠምቆበታል። ስለሆነም አገላብጠውና መዝነው መረዳትን ለማይሹ ችኩሎች የአቤ ነገርና ከረሜላ ጣፋጭ ነው። ግን ደግሞ መርዙ ውስጣቸውን እየበላው ሲሄድ ይረዱታል። እስከዚያ መጠበቁ ግን ተገቢ አይመስለኝም። በእነ አቤ መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎች የተመረዝንና ውስጣችን ያነተብን ሁሉ እነ አቤን በማጋለጥ ከረሜላው ያልደረሳቸውን ልንታደግ ይገባል። ይህም ጽሁፍ የዚሁ የመታደግና የማዳኑ ሥራ አንድ አካልና ጅማሮ ነው። ሌሎቻችሁም በመረዳታችሁ ልክ ልምዳችሁንና ግንዛቤያችሁን በማካፈል የተሰራጩትን መርዞች ብታረክሱ የህሊና እረፍት ይሆናችኋል። የዜግነት ኃላፊነታችሁንም የመወጣት እድል ይፈጥርላችኋል።

አቤ ቶክቻው ቀልድ እያስመሰለና በስላቅ መልክ እንደ ግብረ አበሮቹ ሁሉ ብዙ ዓይነት መርዞችን በፍትህ ጋዜጣ ላይ ተፍቶብናል። በተለይም የተከበሩትን አቶ መለስ ዜናዊ በተመለከተ ከግብረ አበሩ ተመስገን ደሣለኝ ጋር ሆኖ የቀለለበትን መጣጥፎች አንዘነጋም።

አቤን ከሌሎቹ የሚለየው ግን ሥራውን ማወቁ ነው። በጋዜጠኝነት ቆብ የሽብርተኝነት ካባ ለብሰው የነበሩት ግብረ አበሮቹ ሲደረስባቸውና ጎጇቸውን ወህኒ ላይ ሲቀልሱ ሥራውን ጠንቀቆ የሚያውቀው አቤ በፕሬስ አፈና የንስሃ  ስም ነፍሴ አውጪኝ ማለቱ ነው ከግብረ አበሮቹ አቤን የሚለየው። ከዚያም አቤ ባለበት ሆነና ግብረ አበሮቹን ነፃ ለማውጣት ይረዳው ዘንድ ሥርዓቱንና ታጋይ መለስን ማብጠልጠሉን ተያያዘው። መርዘኛ ከረሜላዎቹንም በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣና ፍትህ በኩል ሲያድል

ከረመና የእነ ፍትህ እጣ ፋንታ ሲደመደም በብሎጎችና በማህበራዊ ድረ ገጾች በኩል ሥርጭቱን ይገፉበት ጀመረ።

ሰሞንኛ ልቅምቃሞውንም የለቀቀው በአውራምባ ታይምስ ድረ ገጽ በኩል ነው። ግን ጠብ የሚልና የሚቃረም አንዳች ነገር እንኳን የሌለው ተራ ዝባዝንኬ ነው፡፡ ላልተረዳውና ላልተነደፈው ግን መርዙ ቀላል ያልሆነና ገዝጋዥ ነው።

|ጉዞ ወደ ለንደን ሚጢጢ ማስታወሻ´ ይላል የአቤ መጣጥፍ ርዕስ

አቤ በዋናነት ማውራት የፈለገው በእንግሊዝ አስታኮ ስለኢትዮጵያና ሥርዓቷ ቢሆንም ጥቂት ጊዜ የከተመባትን ኬንያም ጨረፍ አድርጓታል።

ታስታውሱ እንደሆነ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነኝ የሚለው ተመስገን ደሣለኝ ኬንያን ጎብኝቶ አስጎብኝቶን ነበር። ተመስገን በኬንያ ጉብኝቱ እንዳየሁት ብሎ ሲያወራ ኬንያን ከገነት ጋር አስተካክሎና ሕዝቦቿንም ታታሪና የለውጥ ኃይሎች አድርጎ ነበር። ከኢትዮጵያ አንፃር ኬንያን ሲቃኛትም ከመንገዶቿ በስተቀር በእርግጥም ወደፊት እየተምዘገዘገች ያለችና የሚሊኒየሙን ጎል አሳካለሁ ብላ ብትናገር የሚያምርባት እንደሆነች አውስቶናል። ኢትዮጵያንም ከኬንያ አንፃር ሲገልጻት በባዶ የምትፍጨረጨርና የትም የማትደርስ አድርጎ ነበር።

የተመስገን ግብረ አበር ደግሞ  ከኢትዮጵያ ጋር ፍፁም በታሪክም ሆነ በፖለቲካ ዘርፍ፣ በምጣኔ ሀብቱም ሆነ በወታደራዊው መስክ፤ ፍፁም ልትነፃፀር የማይገባትን እንግሊዝ በማንሳት ኢትዮጵያን ማሳነስ ተገቢ ሆኖ ስላገኘው በአንዲት አንቀጽ ብቻ የተመስገንን ገነተ ኬንያ ሲኦልነት በማሳየት ቢያንስ የተመስገንን ኢ ጋዜጠኝነት አረጋግጦልናል። እንዲህም ይለናል።

|...ኬንያውያን መንግሥታቸውን እግዚአብሔር፣ አሜሪካና እንግሊዝ ደግፈው ባይዙላቸው ኖሮ በሙስና ጎርፍ ተጥለቅልቀው አጠገባቸው ያለው ህንድ ውቅያኖስ ውስጥ ይሰጥሙ ነበር።...´

በኢህአዴግ በሚመራው መንግሥት ተሰርተዋል ተብሎ በተቃዋሚውም ሆነ በሁሉም አካላት እውቅና የተሰጣቸው የቤቶች ልማትና የመሠረተ ልማት ግንባታ ዘርፍ መሆናቸው የማይታበል ሀቅ ነው።

ምንም እንኳን እየጨመረ ካለው ሕዝብ አንፃር በቂ ነው ባይባልም የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ ከዓመት ዓመት በቁጥርም፣ በጥራትም፣ በዓይነትም እየጨመሩና እየተሻሻሉ መሄዳቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ተመዝግበው በእጣ ከሚታደላቸው ባሻገር ለልማትና ለከተማ ውበት ሲባል ለሚነሱ ዜጎችም ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የቤት እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው። በቤቶች ልማት ዘርፍ ያለው ጉዳይ የግንባታ ብቻም እንዳልሆነ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ነው። ቤቶቹን ለተጠቃሚዎች

በማስተላለፉ ረገድ የባንክ ብድሮችን ከማመቻቸቱ ጀምሮ ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮችንም ወደተገነቡት መንደሮች ማዳረስ የመንግሥት ድርሻ ነው።

በእኛ አገር አቅምና የምጣኔ ሀብት ደረጃ፣ ልምድና የኀብረተሰብ ግንዛቤ አንፃር እስካሁን የተሰራው ሁሉ ሊበረታታ የሚገባውና በተስፋ ሰጪነቱ ሊወደስ የሚገባው እንደሆነ ብዙዎቹ ይስማማሉ።

አቤ ቶክቻው ግን በሁሉም ዘርፍ አቅሟ ከፈረጠመውና የኬንያም ሳይቀር ነፍስ አባት ያደረጋትን የእንግሊዝ የቤቶች ልማት ዘርፍ ከኢትዮጵያ ጋር በማነፃፀር አገሩን ያኮስሳል።

|…ከአንዲት ሻንጣ በቀር ምንም አልነበረኝምና እቧት ይገፍ ሳልመዘገብ የተሰጠኝ ኮንዶሚኒየም ቤት ውስጥ ገባሁ። ደግነቱ የተባረከ የእንግሊዝ መንግሥት ሙሉ እቃ አሟልቶ ነው የሰጠኝ።…ቤቱ እንደተሰጠኝ የጠቅላይ ሚኒስትር ለቅሶ ላይ በኢቲቪ |መለስ ኮንዶሚኒየም ቤት ሰጥቶ አንቀባሮኛል…´ ብለው ደረት ሲመቱ የነበሩት እናት ናቸው ትውስ ያሉኝ፤ እሳቸው ተመዝግበው እና ስንት ዓመት ጠብቀው በእጣ ላገኙት ቤት ውለታ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሞቱ እንዲያ ደረት ከመቱ እኔ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሞቱ ከአሥረኛ ፎቅ ላይ መፈጥፈጥ አለብኝ ማለት ነው።´

ይኼ ነው እንግዲህ የአቤ ንጽጽር። የማይመሳሰሉና የማይሆኑ ነገሮችን እንደማዳቀል ወይም ያላቻ ጋብቻ ዓይነት ነገር ነው። አሊያም አህያና ጅብን በማጋባት ፈረስ የመጠበቅ ያህል ተራ ንጽጽሮሽና መላ ምት ነው። ዓላማው ግን ኢትዮጵያን ማሳነስ፤ ሥርዓቱን ማንኳሰስ አገሩን ማራከስ በመሆኑ ያቀለለ መስሎት ራሱ የቀለለበት ሀሳብ ነው።

ኢህአዴግና መንግሥት ከተወደሱበት የመሠረተ ልማት ግንባታዎች መካከልም የጎተራው ማሳለጫ ግንባር ቀደሙ ነው። አቤ ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስትራችን ሀዘን ላይ የተገኙ የጎዳና ተዳዳሪዎች ላይ ለማላገጥ ከነበረው ፍላጎት በመነሳት በእንግሊዝ የሚገኙ ማሣለጫዎች ሥር የጎዳና ተዳዳሪ የለም ብሎ ይነግረናል። እንዴትስ ይኖራል? ነው የእኔ ጥያቄ? እንግሊዝማ እንኳንስ ለዜጎቿ ለአቤም የሚሆን ቤት መስጠቷን የነገረን ራሱ አቤ ነው። ለሌላም የተረፈ ቤት ያለበት አገር ላይ የጎዳና ተዳዳሪ ፍለጋ በየማሳለጫው ማማተሩ ታዲያ የጤና ነው የነገር?።

ሌላዋ የአቤ መርዝ የተቀባች ከረሜላ ከተስፋዬ ገብረአብ ጋር ትመሳሰላለች። የብሄርተኝነት መርዝ የተቀባች ከረሜላ ደግሞ እንዲህ ሲል ሊያቀምሰን ይሞክራል።"በእንግሊዝ ጎዳናዎች የተዘዋወርኩበት ባስ የሥራ ቋንቋ ፍሬንና ፍሪሲዮን ሲሆን የሠላም ባስ ግን ትግሪኛ ነው " ይለናል። በእርግጠኛነት አቤ በሠላም ባስ ሄዶ አያውቅም። ቢያውቅኖሮ እንዲህ ዓይነት ስህተት ውስጥ ጭልጥ ብሎ ባልገባ። በሠላም ባስ ተጉዛችሁ ለምታውቁ ሁሉ ዳኝነቱን ትቼ ወደ ሌላው የአቤ መርዘኛ ከረሜላ እሸጋገራለሁ።

አገራችን ለምትከተለው ግብርና መር የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማጫወቻ ሞተሮቹ መሬት፣ ጉልበትና ውኃ መሆናቸው ይታወቃል። የአፈፃፀም ስልቱም (Labour intensive) ነው። አቤ ደግሞ በኤክስፕረስ ባስ ውስጥ ከሹፌሩ በቀርና ከጂኤስ ቴክኖሎጂ (አቅጣጫ ጠቋሚ ድምፅ) በስተቀር አለመኖሩን አድንቆና አወድሶ በሠላም ባስ ውስጥ ያሉ አስተናጋጆችንና ረዳቶችን ብዛት ግን እንደ ኋላ ቀር አሰራር ወስዶ ለመተቸት ይሞክራል።

እንዴት ነው ነገሩ፡፡ አቤ እዚህ አገር ሆኖም ስለ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲከራከር የነበረው ተጠቃሚ ስለሆነም አልነበረም እንዴ? ተጠቃሚ ከነበረ ዘንዳ ደግሞ ቢያንስ ከመንደሩ ሳይወጣ እንኳን እንግሊዝን መገንዘብ እንዴትስ ቢሆን ነው ተስኖት የቆየው? በቴክኖሎጂና በኢንዱስትሪ በልጽገው፤ የአገልግሎት ዘርፉን አልፈው ዛሬ የምጣኔያቸውን መሠረት ኢንፎርሜሽን ካደረጉት አገሮች ጋር የኢትዮጵያን አርሶ አደር እና የትራንስፖርት ዘርፍ ከእንግሊዝ ገበሬ እና ትራንስፖርት ጋር ለማነፃፀር መሞከሩ ሊበሏት ያሰቧትን ካልሆነ በስተቀር ውኃ የማያነሳ ባዶ ሙግት ነው የሚሆነው። ከዚያማ የአቤ ጉድ እንደ ተስፋዬ ገብረአብ ሁሉ ወደ መደምደሚያው ትመጣለች።

የኢትዮጵያ አርሶ አደር የእንግሊዝ አርሶ አደር ዓይነት ቤት፣ መንገድና ትራክተር እንዲኖረው፤ ኢትዮጵያም እንደ አገር እንግሊዝ ላይ በፍጥነት እንድትደርስ ማድረግ የሚገባት በአርሶ አደሩ መንደር የልማት ሠራተኞችና ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችን ማሰማራት ሳይሆን ሽብርተኛ የሆኑት የአቤ ግብረ አበሮች ከእሥር ቤት ሲወጡና ተቃዋሚው ሥልጣን ሲጋራ ወይም ሲይዝ ነው የሚል ዓይነት ይዘት ያለው ማጠቃለያውን ይሰጠናል።

ከዚህ የአቤ ማጠቃለያ ላይ ሁለት ነገር መገንዘብ ይቻላል። የመጀመሪያው አቤ ጋዜጠኛ ሳይሆን የተቃዋሚ ተከራካሪና ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ቀደም ብዬ ለመጠቆም እንደሞከርኩት መጣጥፉ ከመነሻው ስህተትና የማይሆኑ ነገሮችን ያነፃፀረ መሆኑን ነው። እንዳልኩት አቤም |ኢትዮጵያ እንደምን ብትፈጥን ይሆን እንግሊዝ ላይ የምትደርሰው?" ማለቱ መጀመሪያውኑ ሁለት ተመጣጣኝ አገሮችን አለማነፃፀሩን የሚያረጋግጥ ነው። ስለሆነም የማይመጣጠኑ ነገሮችን አነፃፅሮ አንደኛውን ማግዘፍና ሌላኛውን ማኮሰስ ተጠየቃዊ ያልሆነና ፍሬ ከርስኪ ነው ማለት ነው።

አቤም ተናገረ፤ ተስፋዬም አተተ፤ ግብረ አበሮቻቸውም ባገኙት አጋጣሚ መርዘኛውን ከረሜላ በተኑ፤ ኢትዮጵያ ግን አሁንም ታላቅና ታላቅነቷንም በተግባር እያስመሰከረች ያለች አገር ነች።

ሥርዓቱም በሕዝቡ እውቅና ተሰጥቶታል። በሥርዓቱና በሥርዓቱ በሚመራው መንግሥት የተገኙ ድሎችን እና ውጤቶችን ለማጠልሸትና ለማደባየት በእነ አቤ፣ በእነ ተስፋዬና ተመስገን እንዲሁም በውስጥ እና በውጭ ካሉ ግብረ አበሮቻቸው ከመለስ ሞት በፊትና ኋላ ያልተደረገ ሙከራ የለም።

ዳሩ ግን በሁለቱም ወገን የሚወረወረው ድንጋይ በሕዝብ ላይ ነበረና ሕዝብ ደግሞ የሚያስቀድመው የገዛ ጥቅሙን ነውና የነ አቤ ሙከራ በየደረጃው በዜጎችና መንግሥት ከሸፈ። አቶ መለስ ራሳቸው ግለሰብ ከድርጅት በላይ ሊሆን እንደማይችል በተናገሩት መሠረት መለስ የኢህአዴግ ውጤት ናቸው፡፡ ሥራቸውም የኢህአዴግን ፕሮግራም ማስፈፀም ነበር። ስለሆነም እነ አቤ በሚሉት መሠረት መለስን ከኢህአዴግ በመነጠል በነጻ የሚታደለው ከረሜላ መርዛማ ነው ማለት ነው። መለስን የወደደ ሁሉ ኢህአዴግን እንደሚወድ መጠራጠር የለብንም።

ኢህአዴግ ከዚህም በኋላ ችግሮቹን እያስወገደና እየጠነከረ የሚሄድ ድርጅት ሊሆን እንደሚችል እንደ ማዕበል የተቸረው የሕዝብ ድጋፍ ያረጋግጥልናል። ከኢህአዴግና ከመንግሥት አሁን የሚጠበቀው ብዙ ርቀት ያልተጓዙበትን የመልካም አስተዳደር ችግር እየፈታ የሕዝቡን ድጋፍ ሳያባክን ይዞ መቀጠል ብቻ ነው።

በሥርዓቱ መሪ ሞት የታየው የሕዝብ ድጋፍ ሥርዓቱ የበሰለ እንደሆነ የሚያመላክት እንደመሆኑ ኢህአዴግ በዚህ ድጋፍ ሳይኩራራ በማያቋርጥ ሥራ ውስጥም መስጠም አለበት።

ተቃዋሚው ኃይልና እነ አቤ እንደሚሉት ሥርዓቱ በመለስ ላይ ብቻ ተገንብቶ ቢሆን ኖሮ ያየነውን ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግርና የተረጋጋውን ሕዝብ ለመመልከት ባልታደልን ነበር። ነገር ግን ከመለስ ሞት በኋላ ኢህአዴግ በነበረው ቁመና ሥርዓቱ በመለስ ላይ የተንጠለጠለ ሳይሆን የተደራጀና ተቋማዊ መሠረት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ይህንኑም ምዕራባውያን ጭምር ያረጋገጡት ነው።

ሩቅ ሳንሄድ ሰሞኑን ብሉምበርግ በዘገባው "የዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (አይ.ኤም.ኤፍ.) ኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ግንባታዋን እንድታቀዛቅዝ አዟል" ቢልም አይ.ኤም.ኤፍ. አድርጎት በማያውቀው ሁኔታ "አላልኩም አላዘዝኩምም" ሲል ማስተባበሉ የኢህአዴግን ጥንካሬና ብስለት፤ የአገራችንን ደረጃ ከፍታም የሚያሳይ ይመስለኛል።

በተደጋጋሚ እንደሚገለፀው በሰብዓዊ መብት ጥላ ሥር ለሌላ ተልዕኮ የሚንቀሳቀሰው ሂዩማን ራይትስ ዎች ከመለስ ሞት በኋላ ኢትዮጵያን ለመጠምዘዝ ጊዜው አሁን ነው የሚል መልዕክት በዳይሬክተሩ በኩል ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ቢያስተላልፍም መለስ ከሞተ ወር ከምናምን እንኳን ሳይቆይ የዓለም ባንክ 1 ነጥብ 15 ቢሊዮን ዶላር ከወለድ ነፃ ለኢትዮጵያ ማበርከቱ የሥርዓቱን መረጋጋትና ጥንካሬ ቢያመለክተን እንጂ እነ ተስፋዬና አቤ የሚሉትን የበሬ ወለደ ሽኩቻ የሚያሳይ አይደለም።

500 ሚሊዮን ዶላር ለሁለት የስኳር ፋብሪካ ግንባታዎች የቻይና መንግሥት የለገሰን ከመለስ ሞት በኋላ ነው። የሁለቱ ሱዳኖችም ጉዳይ መለስ ከሞተማ አበቃለት ቢባልም የተፈለገውን ውጤት ይዞ የተቋጨው ከሰሞኑ ነው። የሶማሊያም ጉዳይ ቢሆን ከመለስ ሞት ኋላም ከሐዲዱ አላፈነገጠም። መለስ ሥርዓት ገንብቶ በማለፉ ከጀርባ ባለው የሕዝብ ድጋፍ ሥርዓቱ የበለጠ እየጠነከረ ሊሄድ እንደሚችል እያየን ነው።

የነውጠኛው ቅንጅት አካል የነበረው ዳንኤል በቀለና መሰሎቹም ሰሞኑን በተደረገው የዓለም ባንክ ድጋፍ በመብከንከናቸው ረጂና ደጋፊ የሆኑ ተቋማትንና አገራትን ሲዘልፉ፤ እንደነ ስየ ዓይነት ብልጣ ብልጦች  ደግሞ የሕዝቡን ድጋፍ የሚሻገሩበት አማራጭ በማጣታቸውና በሸኩቻ ሥልጣን እንደማይገኝ በመገንዘባቸው የብሄራዊ እርቅና የሥልጣን ሽግግር እየጠየቁ ነው። አሁን የተቃዋሚው እና በጋዜጠኛ ቆብ ሌላ ካባ የደረቡ አመፀኞች ሰፈር ተመናምኗል። ድጋፍና ጊዜ ሰጪው ሕዝብ እንጂ እነ ኤሊያስ ክፍሌ አለመሆናቸው ተረጋግጧል።

ሕዝቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበሰለና ምክንያታዊነቱን በተግባር እያሳየ ነው። ስለሆነም ዛሬ ሕዝቡ ተቃዋሚን እንደ ተቃዋሚ የማዳመጥና እውቅና የመስጠት ችግር የለበትም። በዚሁ ላይ በተቃዋሚ ስም ሌላ ካባ የደረቡ ጽንፈኞችንም የመነጠል አቅሙንም የገነባ በመሆኑ አሁን በእነ ተስፋዬና አቤ ቶክቻው፤ በእነ ኤሊያስ ክፍሌና ዳንኤል በቀለ፤ በሂዩማን ራይትስ ዎችና በቪ.ኦ.ኤ በነፃ የሚበተኑትን መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎች የሚልስበት ምላስና ግለሰቦቹንም የሚሸከምበት ትከሻ የለውም ።

ኢህአዴግና በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት አሁንም ህግና ሥርዓትን የማስከበር ጉዳይ ለድርድር የሚቀርብ እንዳልሆነ ግልጽ አቋም በመያዝ ለዚህ ሕዝብ ሊሰሩና ሰርተው ሊያሰሩት ይገባል።